# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 203 መጋቢት 27 2004 ገጽ 1


**ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ የቁጥር ማምታታት ሙያዊ እገዛ የሚያደርጉ "ምሁራን" ዛሬ በሚሠሩት ሥራ ነገ የሚያፍሩ መሆኑን ማስታወስ ይፈልጋል። ሥራቸው ከማሳፈርም አልፎ የሚያስጠይቅ እንደሆነ እንዲገነዘቡ እንፈልጋለን።**

**የመለስ ዜናዊ ባለሟሎች ሆይ! አድምጡን!!! መቸ ነው እናንተ በቁጥሮች መዋሸት የሚሰለቻችሁ? መቼ ነው ለህሊናችሁ ተገዥ የምትሆኑት?**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ከደቡቡ የአገራችን ክፍል የተባረሩ የአማራ ተወላጆች ታፍሰው ወደ ተለያዩ የማጎሪያ ካምፖች መወሰዳቸው እያነጋገረ ነው

የወያኔ የዘረኝነት ፖሊሲ ሰለባ የሆኑ ከደቡብ ክልል ቤንች ማጅ ዞን ጉራፋርዳ ወረዳ በግፍ ተፈናቅለው ወደ አዲስ አበባ የመጡ ወደ 200 የሚጠጉ የአማራ ተወላጆች ተጠልለው ይገኙበት ከነበረው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ቅጥር ግቢ ውስጥ ራሱን የብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ/ብአዴን/ ብሎ በሚጠራው የወያኔ ተቀጽላ ድርጅት ካድሬዎች ተገደው እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ ከማንም ጋር ሊገናኙ ወደማይችሉበት የተለያዩ ማጎሪያ ካምፖች መበታተናቸዉንና ከፊሉ በፖሊስ ሃይል ተገደው ወደ ደብረብርሃን መወሰዳቸ ተዘገበ።

ተፈናቃዮቹ ወደ አዲስ አበባ እንደመጡ በስላሴ ቤተክርስቲያን ለመጠለል ነበር ጥያቄ ያቀርቡት፣ ይሁንና በችግር ጊዜ መጠለያ ትሆናለች ተብላ የምትታመነዋ ቤተክርስቲያን አላውቃችሁም ብላ አሰናብታቸዋለች፤ ህዝበ ክርስቲያኑም በቤተክርስቲያኒቱ መልስ በእጅጉ አዝኖ ሰንብቷል። በጉዳዩ የተበሳጨው መኢአድ ሁሉንም ስደተኞች ወስዶ በግቢው ውስጥ ሰፊ ድንኳን በመትከል ሲንከባከባቸው ቆይቷል። ጉዳዩ የመገናኛ ብዙሀን ትኩረትን ከሳበ በሁዋላ በአዲስ አበባ እና በመላው አገሪቱ ከፍተኛ የሆነ ቁጣ ከመቀስቀሱ ሌላ የከተማው ቀዳሚ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ ሰንብቷል።ይህንንም ተከትሎ በአገር ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶች በውጭ አገር ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጋር በመነጋጋር ተፈናቃዮችን ለመርዳት ሰፊ የእርዳታ ማሰባሰብ ዝግጅት እያደረጉ ባሉበት ሰዓት፣ ሲፈናቀሉ አላውቃችሁም ያላቸው ብአዴን ተፈናቃዮች ከመኢአድ ግቢ እንዲወጡ አድርጓል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በኢንቨስት መንት ሥም ዜጎችን ከይዞታቸው የማፈናቀሉ ዘመቻ ቀጥሎአል። ከመሬታችን አንፈናቀልም ያለው የአፋር ህዝብ ከወያኔ መከላከያ ሰራዊት ጋር ተፋጧል

ለዜጎች ህይወትና ደህንነት ደንታ የሌለው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ የአዋሽ ወንዝ ተፋሰስን የኑሮው መሰረት አድርጎ የኖረውን የአፋር ህዝብ ከቦታው በማፈናቀል የሸንኮራ ተክል ልማት ለማስፋፋት እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ ከፍተኛ ህዝባዊ ተቃውሞ እንደገጠመው ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰን መረጃ አመለከተ።

ካለፈው ሁለት ሳምንት ወዲህ እጅግ እየተጠናከረ በመጣው ህዝባዊ ተቃውሞ የተደናገጠው የወያኔ አገዛዝ ተቃውሞውን በሚያሰማ የአካባቢው ህዝብ ላይ ሰራዊት በማዝመት የሃይል እርምጃ እንደወሰደና በዚህም ምክንያት እርጉዝ ሴቶች፤ ወጣቶችና አዛውንቶች ሳይቀሩ የጥቃቱ ሰለባ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሎአል።

ተቀማጭነቱ ቤልጂዬም ብራስልስ የሆነው የአፋር ሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት ሃላፊ የሆኑት አቶ ገአስ አህመድ ኑር በክልሉ ህዝብ ላይ እየደረሰ ስላለው መብት ረገጣና መፈናቀል ለዝግጅት ክፍላችን ሲያስረዱ፤ ከህዝቡ ፈቃድና ፍላጎት ውጪ ህዝቡን ለኑሮውና ህይወቱ መሰረት ከሆነው የአዋሽ ወንዝ ተፋሰስ ክልል ለማፈናቀል በመወሰድ ላይ ያለውን እርምጃ የተቃወሙ ሁለት ነፍሰ ጡሮችን ጨምሮ 8 ሴቶችና ቁጥራቸው የበዛ ወንዶች ታስረዋል። በእስር ላይ እያሉና ወደ እስር ቤት ሲወሰዱ ድብደባ የተፈጸመባቸው ሰዎች ቁጥርም ቀላል እንዳልሆነ የገለጹት አቶ ገአስ የአካባቢው ተወላጆችን መኖሪያ በሃይል ለማፍረስ የተሰማሩ ዶዘሮችን ለማስቆም ሙከራ የሚያደርግ ማንኛውም ሰው ላይ በክልሉ የተሰማራው መከላከያ ሰራዊት የፈለገውን እርምጃ እንዲወስድ መታዘዙን ከአካባቢው ምንጮቻቸው መረጃ እንደደረሳቸው ገልጸዋል።

በመከላኪያ ሠራዊቱና በህዝቡ መካከል በተፈጠረው ግብግብ ፍርሃትና ስጋት የገባው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በቦታው ያሰማራቸውን ዶዘሮች ለማስጠበቅ ያሰማራቸው ሃይሎች አንድ ኝጹህ ዜጋ ተኩሰው እንዳቆሰሉ ሆኖም ህዝቡ ለህይወቱና ለኑሮው ብቸኛ የሆነውን ይዞታውን አቅሙ እስከፈቀደ ድረስ ለመከላከል በህይወቱ ወስኖ እየተጋፈጠ እንዳለ ለማወቅ ተችሎአል።

ከአካባቢው በደረሰን ተመሳሳይ ዜና በዚህ የወያኔ ዜጎችን ከቦታቸው የማፈናቀል ዘመቻ ቁጥራቸው ከሰባ ሺ በላይ የሆነ የአፋር (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ ቡድን ከደቡብ ያባረራቸውን ዜጎች በግዳጅ ወደ ትውልድ መንደራቸው እየላከ መሆኑ ተዘገበ። ግንቦት 7 ድርጊቱን የዘር ማጥፋት እርምጃ ነው ሲል በመኮንን መግለጫ አውጥቶአል

በዘር ጥላቻ ተጸንሶ ለስልጣን የበቃው የዘረኛው መለስ ዜናዊ ቡድን ስልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ በአማራው ህዝብ ላይ እየወሰደ ያለውን የበቀል እርምጃ በማጠናከር በሰላም ሰርተው ይኖሩበት ከነበረው የደቡብ ክልል በቅርቡ ያባረራቸውን በሃይል ወደ ትውልድ መንደራቸው እየመለሳቸው መሆኑን ሰንደቅ የተባለው ጋዜጣ ዘገበ።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን ለማስፈር አቅም ያለውን ለምና ድንግል መሬታችንን ለባዕዳን አሳልፎ በመስጠት ሥራ የተጠመደው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ አገሬ ነው ብሎ ከሰሜኑ ክፍል ወደ ደቡብ ተጉዞ የሰፈረውን የአማራ አርሶ አደሮች የለፉበትን ሃብትና ንብረት ቀምቶ ባዶ እጃቸውን ማባረሩ ፤ የአገዛዙ በአማራ ህዝብ ላይ ያለው ጥላቻና ቂም ከ21 አመት የስልጣን ቆይታ ቦኋላም ቢሆን አለመብረዱን ያሳያል የሚሉ በዙዎች ናቸው።

የአማራውን ህዝብ ጥቅም አስጠብቃለሁ በማለት በስሙ የተደራጀውና በየዋህ አማሮች የህይወት መስዋዕትነት ለጸረ ህዝብ ሃይሎች አገልግሎት እየሰጠ ያለው ብአዴን እነዚህን ከቤንች ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ የተባረሩትን የአማራ ተወላጆች አስገድዶ ወደ ትውልድ መንደራቸው በማጓጓዝ ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወተ መሆኑን ሰንደቅ በዘገባው አመልክቶአል።

ወያኔ የአማራ አርሶ አደሮችን ሰርተው ከሚኖሩበት መሬታቸው አፈናቅሎ "ወደ አገራችሁ ሂዱ" ብሎ በግዴታ ወደ የትውልድ መንደራቸው ማባረሩ በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ ከፍተኛ የሆነ ተቃውሞ ቀስቅሶአል። ይህንን የወያኔን የጥፋት እርምጃ በመኮነን ንቅናቄያችን ግንቦት 7 በትናንትናው ዕለት ተጨማሪ መግለጫዎችን በአማሪኛና በእንግሊዜኛ ቋንቋዎች አውጥቷል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግንቦት 7 በዘረኛው ወያኔ ከደቡቡ የአገራችን ክፍል እየተባረሩ ያሉትን የአማራ ተወላጆች አስመልክቶ ያወጣውን መግለጫ ሙሉ ቃል በገጽ 2 ያንብቡ።

## በኢትዮጵያ ውስጥ እየደረሰ ያለው የመብት ጥሰትና የህጋዊ ስርዓት መናጋት በእጅጉ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን የኢትዮጵያ ፌደራላዊት መድረክ አስታወቀ

ድርጅቱ ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ ወያኔ ስልጣን ከተቆናጠጠበት ጊዜ አንስቶ የዜጎች መብት ጥሰት እየባሰበት መጥቷል፤ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የህግ የበላይነት አለ ማለት አይቻልም፤ለመብት ጥሰት ሳይጋለጡ ለመኖር የወያኔ ድርጅት አባል መሆን የግድ ሆኗል ብሏል።

እንደ መግለጫው በዘረኛው መንግስት ካድሬዎች ከህግ አግባብ ውጪ ዜጎች ይታሰራሉ፤ ከስራ ይፈናቀላሉ፤ንብረታቸው ይዘረፋል፤ በአጠቃላይ ግፍና በደል ይፈጸምባቸዋል።በመሆኑም መድረክ ህግ የት አለ? በወረቀት ላይ መኖሩ ፋይዳው ምንድነው? እንዲል ተገዷል።

የመድረክ መግለጫ በዘረኛው የወያኔ መንግስትና ሆድ አደር ካድሬዎቹ ተፈጸሙ ያላቸውን በርካታ በደልና ግፎች የዘረዘረ ሲሆን በተለይም የኦሮሞ ፌደራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅንቄ /ኦፌዴን/ በሚንቀሳቀስበት የኦሮሚያ አካባቢ እየተፈጸመ ያለውን ግፍ እጅግ ዘግናኝ ብሎታል።

በኦሮሚያ በቄለም ወለጋ ዞን፣በሆዋ ገላንና በሆዋ ወለል ወረዳዎች ውስጥ ሰላማዊ ዜጎችን ሌቦች በማለት የስርዓቱ ሚሊሻዎችና ፖሊሶች ከባድ ድብደባ እንደፈጸሙባቸው የሚያብራራው መግለጫው በተለይም ሰንበቶ ወዬሳ፣ይልቅ እስራኤል፣ደገፉ ሲርጋና ወሰኑ ዲሳሳ በተባሉ ሰላማዊ ዜጎች ላይ የተፈጸመውን ሰቆቃ ለአብነት ያነሳል።

እነዚህ ዜጎች በቅድሚያ ታስረው በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል።በመቀጠልም ሰብዓዊ ክብራቸውን በማዋረድ በገበያ ውስጥ እየዞሩ እንዲገረፉ ተደርጓል።ይህም ይላል መግለጫው በ21ኛው ምዕት ዓመት ወያኔ ይህቺን ሀገር ወደ ጥንታዊው ኋላ ቀር ስርዓት እየወሰዳት መሆኑን አመላካች ነው።

በተመሳሳይም በሁዋ ወለል ወረዳ የጉራቴ ወለል ቀበሌ ነዋሪ የሆነው ረጋሳ ቲኾ በቶጂ ወረዳ ፖሊስ በደረሰበት ድብደባ ህይወቱ ማለፉንና በባለቤቷ ሞት የተበሳጨችው ወይዘሮ ተመስጌ ሊሙም በዕለቱ ራሷን ሰቅላ መሞቷ በመግለጫው ተብራርቷል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የመለስ ባለሟሎች፤ መቼ ነው በቁጥሮች መዋሸት የሚሰለቻችሁ?!

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ባለሟሎች ኢትዮጵያ ውስጥ ድህነት በከፍተኛ ሁኔታ መቀነሱን የሚያረጋግጥ "ጥናት" ይፋ አደረጉ።

እንደ መለስ ባለሟሎች "ጥናት" ውጤት ከሆነ ከ1997 ዓም ጋር ሲነፃፀር በ2003 ዓም በመላ ሃገሪቱ ድህነት በ23.5 በመቶ ቅናሽ አሳይቷል። ተበትኖ ይታይ ከተባለም የከተማ ድህነት በ 26.9 በመቶ፤ የገጠሩ ደግሞ በ22.7 በመቶ ቅናሽ አሳይቷል ተብሏል። እንዲህ ዓይነት ፈጣን የድህነት ቅነሳ በዓለም ታሪክም ብዙ የሚታወቅ አይደለም።

"ጥናቱ" ድህነት በ1997 ከነበረበት 38.7 በመቶ ወደ 29.6 በመቶ ወርዷል። ይህ ማለት ደግሞ ኢትዮጵያ ድህነትን በግማሽ የመቀነስ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግብ ታሳካለች ይላል። "ጥናቱ" የተፈለገውም ለዚህ ነው።

የእምነት ቦታዎችን የሞሉትንና ጎዳናዎችን ያጣበቡትን ነዳያንን፤ በምግብ እጥረት ክፍል ውስጥ አዙሯቸው የሚወድቁ ህፃናትን፤ ከድህነትና ከአፈና ለማምለጥ በባህር የሚሰጥሙትን እና በበረሃ ቀልጠው የሚቀሩ ወጣቶችን፤ ከክልላችሁ ውጭ ሰፍራችኋል በሚል የተፈናቀሉ ምስኪኖችን፤ እና የመሳሰሉትን እየዘረዘርን የመለስ ባለሙያዎች የለፉበትን "ጥናት" መሞገት አንሻም። በየጊዜው እያሻቀበ መያዣ፣ መጨበጫ የታጣለት የዋጋ ንረት የፈጠራቸውን አዳዲስ ድሆችን ብዛት በማስታወስም "ጥናቱን" ማጣጣል አንፈልግም። እርዳታውም ድጎማውም አልበቃ እያለ ከውጭ አገራት እየተገዛ የሚገባው የስንዴ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ ከምን የመጣ ነው ብለን መጠየቅም አያሻም።

ከመለስ ዜናዊ ባለሟሎች የምንፈልገው የሚከተለውን ቀላል የትርጉም ማብራሪያ ብቻ ነው።

### *ለመሆኑ "ድሃ" ማነው?*

ይህ መሠረታዊ ጥያቄ መሆኑ "ተመራማሪዎቹም" አልጠፉቸውም። ስለዚህም የድህነትን ትርጉም በቁጥሮቹ መሃል በጥንቃቄ ሸንቁረውታል። በመሆኑም ቁጥሮቹን ፈልፍለው ካልፈለጉ ፊት ለፊት አይገኝም። ይህ ነው የመለስ ዜናዊ ባለሟሎች የተካኑበት ሙያ።

የመለስ ዜናዊ ባለሙያዎች በስፋት የሚሠራበትን በቀን የአንድ አሜሪካን ዶላር ገቢን እንደ ድህነት መመዘኛ መውሰድን አጣጥለው ጣሉት። ዝቅተኛው የድህነት ወለል በቀን ከ 2,200 ካሎሪ በታች መመገብ ነው አሉ። ይህም ምንም የሚያጣላ ነገር አይደለም። ትልቁ ጨዋታ ያለው 2200 ካሎሪ ይገዛል ባሉት የገንዘብ መጠን ነው። በእነሱ ስሌት2 200 ካሎሪ ምግብ በ5 ብር ይሸመታል። ሃቁ ግን 5 ብር 2200 ካሎሪ የያዘ ምግብ ሩቡን እንኳን የማይገዛ መሆኑ ነው። 2200 ካሎሪ ለማግኘት ወደ 1 ኪ.ግ የሚጠጋ የጤፍ ዱቄት ያስፈልጋል። ጥሬው ጤፍ ይቃም ቢባል እንኳን በአሁን ገበያ ወደ 15 ብር ይጠይቃል። ጤፉ መፈጨት፣ መቡካት፣ መጋገር እና ማባያ የሚያስፈልገው ከሆነ ደግሞ ዋጋው በጣም ይጨምራል።

የመለስ ዜናዊ "ባለሙያዎች" ግን 2200 ካሎሪ በ5 ብር ይገዛል ብለው ወስነው የድህነት ወለል በዓመት ብር 1985.00 ማግኘት ነው ሲሉ ደመደሙ። እናም "ሳይቲስቶቹ" አዲስ የድህነት ትርጓሜ አመጡ። አዲሱ የመለስ ዜናዌ የድህነት ትርጓሜ እንደሚከተው ይነበባል።

### *ድሃ ማለት በቀን 5 ብር እና ከዚያ በታች የሚያገኝ ሰው ማለት ነው።*

የመለስ ዜናዊ "ሊቃውንት" ድህነትን እንዲህ አዲስ ትርጉም በመስጠት ቀነሱት። የሚያሳዝነው 29.6 በመቶ የሆነው የአገሪቱን ዜጋ ማለትም አንድ ሶስተኛ የሃገሪቱን ህዝብ በዚህ ዓይነቱ ትርጓሜ እንኳን ከድህነት መውጣት አለመቻሉ ነው። ይህ ራሱ ሊያሳዝናቸውበተገባ፤ እነሱ ግን በደስታ እየፈነጠዙ ነው።

የመለስ ዜናዊ "ሊቃውንት" የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ከወያኔ "ተራራ አንቀጠቀጥን" ጉራ ጋር ተመሳሳይ ነው። መለስ ዜናዊ ከበረሃ ጓደኞቹ በሰማው "የቆረጣ ስልት" ዛሬ ድህነት እያጠፋ ነው። በዚህ ስልት መሠረት ድህነትን ለመቀነስ የግብርናና የኢንዱስትሪን ምርቶችን ማስፋፋት፤ ተጨማሪ የሥራ እድሎች መክፈት፤ ወይም የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ግድ አይደለም። በመለስ ዜናዊና በሊቃውንቱ "ግኝት" መሠረት ድህነትን ትርጉሙን ብቻ በመቀየር ድራሹ ማጥፋት ይቻላል።

እንዲህ በትንሽ የትርጉም "ማስተካከያ" ይኸን የመሰለ ውጤት መገኘቱ አበረታች ነው። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ነገ "ድሃ ማለት በሳምንት አንድ ጉርሻ መቅመስ የማይችል ማለት ነው" ብሎ በመተርጎም እንደ ምርጫ 2002 ውጤት "99.6 በመቶ የኢትዮጵያ ህዝብን በድህነት ወለል በላይ ማድረግ ችለናል" ብሎ ማወጅ ይቻላል። በቁጥር መጫወት የማይሰለቻቸው "ምሁራን" እስካሉ ድረስ ይህንን ቀባብቶ አሰማምሮ ማቅረብ አያቅትም።

ይህ የድህነት ቅነሳ "ጥናት" የመለስ "ፈጣን እድገት "ምንጭ" ምን እንደሆነ ቁልጭ አድርጎ ያሳየ ሆኗል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ለመለስ ዜናዌ አገዛዝ የቁጥር ማምታታት ሙያዊ እገዛ የሚያደርጉ "ምሁራን" ዛሬ በሚሠሩት ሥራ ነገ የሚያፍሩ መሆኑን ማስታወስ ይፈልጋል። ሥራቸው ከማሳፈርም አልፎ የሚያስጠይቅ እንደሆነ እንዲገነዘቡ እንፈልጋለን።

የመለስ ዜናዊ ባለሟሎች ሆይ! አድምጡን!!! መቸ ነው እናንተ በቁጥሮች መዋሸት የሚሰለቻችሁ? መቼ ነው ለህሊናችሁ ተገዥ የምትሆኑት? ቆም ብላችሁ ራሳችሁን ታዘቡ። መስመራችሁንም አስተካክሉ። ይህን ማስታወሻ ችል አትበሉ፤ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሊሆን ይችላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

................................................................................................................................

## ምን እስከንሆን ነው የምንጠብቀው?

ከግንቦት 7 የተሰጠ መግለጫ መጋቢት 27 2004 ዓ.ም

መለስ ዜናዊ "የኢትዮጵያን አጥፍቼ ልጥፋ" ስትራቴጂ ሰሞኑን በሙሉ ኃይሉ ሥራ ላይ እየዋለ ነው። ከዓመታት በፊት በመንግሥት ውትወታ በደቡብ ክልል ሰፍረው የነበሩ የአማራ ዝርያ ያላቸው አርሶ አደሮች ወንጀለኞች የሆኑ ይመስል ንብረታቸው ተዘርፎ እንዲባረሩ ወያኔ ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት እየደረሰባቸው ያለው ግፍ ዓለም አቀፍ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ሆኗል።

ግንቦት 7: የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከጥቂት ሣምንታት በፊት እንዳስታወቀው በወያኔ ዓይን ያወጣ ዘረኛ ውሳኔ ምክንያት በሺዎች የሚቆጠሩ የአማራ ተወላጅ የሆኑ ገበሬዎች ለዓመታት ሲያርሱት የነበረው መሬት እና በብዙ ድካም ያፈሩት ጥሪት ተነጥቀዋል። እነዚህ አርሶ አደሮች በወያኔ ታጣቂዎችና ወታደሮች ተደብድበዋል። እንደ ባእድ "ወደ አገራችሁ ተመለሱ" ተብለው በገዛ አገራቸው ውስጥ ስደተኞች ሆነዋል። በዚህም ምክንያት በሺዎች የሚቆጠሩ የአማራ ገበሬዎች መውደቂያ አጥተው ከነልጆቻቸው ጎዳና ላይ ተጥለዋል።

ግንቦት 7፡ በአማራ አርሶ አደሮች ላይ እየደረሰ ያለው ጥቃት የወያኔ ዘረኝነት ፓሊሲ ውጤት መሆኑን ብቻ ሳይሆን እርምጃዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል ነው ብሎ ያምናል። ስለሆነም በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ከተገፉትና ከተሰደዱት የአማራ ገበሬዎች ጎን እንዲቆም ጥሪ ያደርጋል።

አማራውን እወክላለሁ የሚለው የብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) የመለስ ዜናዊ ምርጥ ባርያ ለመሆን ሲል በአማሮች ላይ ዘምቷል። ብአዴን የወያኔን ጥቃት አቀነባባሪና አስፈፃሚ ሆኗል። ሌላው ቀርቶ ከደቡብ ክልል የተፈናቀሉ የአማራ ድሃ አርሶ አደሮች አዲስ አበባ ከተማ እንዳይገቡ ከመንገድ እያፈሰ ወደ ማጎሪያ እስር ቤቶች የሚልከው ብአዴን ነው። ወያኔ በመላው ኢትዮጵያ በተለይም በአማራ ላይ እንዲፈነጭ ብአዴን የተጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። ስለሆነም በአማራ ላይ እየተፈፀመ ላለው ወንጀል ብአዴንም ቀንደኛ ተጠያቂ ነው።

በጥንታዊው እና ታሪካዊው የዋልድባ ገዳም ላይ እየተደረገ ያለው ጥቃትም ከዚሁ ጋር መታየት ያለበት ጉዳይ ነው። ዋልድባ በዶዘር መታረስ ጀምሯል። አቤት ለማለት የቃጡ አርሶ አደሮችና መነኮሳት በመለስ ዜናዊ ቅጥረኖች ተንገላተዋል። ይህ ሃይማኖትን፣ ቅርስን፣ ታሪክን መድፈር ነው።

አማራ የእርሻ መሬቱ ተነጥቆ ከፊሉ ለትግራይ፣ ከፊሉ ለሱዳን፣ ከፊሉ ደግሞ ባህር ተሻግረው ለመጡ ቱጃሮች ተከፋፍሏል። ድሃው አማራ ምን ይሁን?

እውን እኛስ ከዚህ በላይ ምን እስክንሆን ነው የምንጠብቀው?

ወያኔ ለማንም የማይመለስ መሆኑ የእለት ተእለት ተግባሩ ገላጭ ነው። ቁጥራቸው 22 ሺህ በሚሆኑ የአማራ ድሃ ገበሬዎች ላይ የደረሰው በአፋር አርብቶ አደሮችም ላይ ደርሶ እያየነው ነው። በወያኔ ወገኖቻችንን ከመኖሪያ ቀያቸው የማፈናቀል ዘመቻ ሳቢያ ከጉራ ፈርዳ ወረዳ እንዲፈናቀሉ ከተደረጉ የአማራ ወገኖቻችን በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት ከ70 ሺህ በላይ የአፋር ወገኖቻችንም ከትውልድ መንደራቸው በወታደር ኃይል እየተባረሩ ነው።

ዛሬ በአማራ አርሶ አደሮች ላይ የደረሰው ከይዞታቸውና ከቄያቸው መፈናቀል ትናንት በጋምቤላ ወገኖቻችን ላይ ደርሶ አይተናል። በኦሮሚያም በደቡብም እንዲሁ። ሁኔታው በዚሁ ከቀጠለ ነገ ሁላችንም ተነሺዎች፤ ሁላችንም ተሰዳጆች ነን።

እናም ደግመን እንጠይቃለን።

### *ምን እስከሚሆን ወይም ምን እስከምንሆን ነው የምጠብቀው?*

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፀነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔ መወገድ አለበት ብሎ ያምናል። በግንቦት 7 እምነት ወያኔን ሳናስወግድ በወገኖቻችን ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ ማስቆም አንችልም። የወያኔን ግፍ ማስቆም የሚቻለው በተናጠል ትግል ሳይሆን በጋራ ስንቆም መሆኑን ለአፍታም አንዘንጋ።

ግፍ በዝቷል። መሮን ከፍቶን እንነሳ!!! ይህን ግፍ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲያበቃ የምችሹ ሁሉ ከግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ጎን እንድትቆሙ ጥሪ እናደርጋለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## በህግ አምላክ ወድቃ በተነሳችው ባንዲራ፣

የግንቦት 7 ድምጽ ጋዜጣ በቁጥር 12 ነሃሴ 1 2000 ዓ ም ህትመቱ በርዕሰ አንቀጽነትነት አስፍሮት ከነበረው የተወሰደ

መብት እንዲከበር፣ ፍትህ እንዲሰፍን፣ ህዝብ የህገሩና የገዛ ህይወቱ ባለቤት እንዲሆን ለተደረገው ትግል፣ ወላጆች ውድ ለጆቻቸውን፣ ሚስቶች ባሎቻቸውን፣ ባሎች ሚስቶቻቸውን፣ እህቶች ወንድሞቻቸውን፣ ወንድሞች ደግሞ እህቶቻቸውን ገብረዋል። ትግሉ የመብት ብቻ ሳይሆን፣ ከድህነት ከበሽታና ከመሃይምነት ለመላቀቅ ነበር። ይሁንና ያ ሁሉ የእንባና የደም መባ ተከፍሎ የሀገራችን ህዝብ አልሞ ከተነሳውና በነጻነት ወዳድነቱ ለዘመናት ሲከፍለው ለኖረው መሰዋዓትነት የሚመጥን መንግስታዊ አስተዳደር መመስረት አልቻለም። ድህነትና በሽታን የማጥፋት ህልሙ በኗል። ባለንበት ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ የተከመረበትን የህይወት አሳርና መከራ ላጤነ፣ “እንዴት በአንድ ሀገርና ህዝብ ላይ እንዲህ ማለቂያ የሌለው የመዓት ዶፍ የወርዳል?” የሚል የአግርሞትና የሃዘን ጥያቄ የሚያስነሳ ነው።

ህዝብ ለህግ የነበረው ተስፋ ምን ያህል ሥር የሰደደ እነደነበረ በየአደባባዩ ወንጀልን፣ ጥቃትንና በደልን ለማስቆም፣ “በህግ ዓምላክ” የሚለውን የተበዳይ ጬኅት እናስታውሳለን። ሌላው ተበዳይ ግለሰብ በአደባባይ ያሰማ የነበረው ጬኅት “ወድቃ በተነሳችው ባንዲራ “ የሚለው ነበር። ለአምስት የጣሊያን ወረራ ዓመታት ነጻነቱን አጥቶ፣ በሃገሪቱ መናገሻ ከተማ የሃገሩን ባንዲራ ሳይሆን የፋሽስት ጣሊያን ባንዲራ ሲወለበለብ ያየ ህዝብ ለነጻነቱ መመለስ ለሰጠው ታላቅ ትርጉም ነበር ይህ አባባል የተወሰደው። “ወድቃ በተነሳችው ባንዲራ በህግ ዓምላክ” ለኢትዮጵያ ህዝብ የነበራቸው ትርጉም አንድ ነበር። ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለፍትህና ለነጻነቱ ትልቅ ትርጉም የሚሰጥ በመሆኑ ተበዳይ፣ በዳይን በህግና በባንዲራ ሥም መገዘት ይችላል የሚል ጠንካራ ዕምነት የነበረበት ሁኔታ የሚያሳይ ነው።

እንደእውነቱ ከሆነ “በህግ ዓምላክ፣ ወድቃ በተነሳችው ባንዲራ አትንቀሳቀስ ብያለሁ” በሚል ትዕዛዝ አንድ ግለሰብ ሌላውን ቀጥ አድርጎ ያስቆም እንደነበር የምናስታውስ ብዙዎች ነን። ከሁሉም በላይ ግን ሁላችንም የሃገሪቱን ተገዥዎች ለከፊ ሃዘንና ብስጭት የዳረገን በህዝብ ቁስል ጭራሮ መስደድ የማያልቅበት የመለስ ዜናዊ አምባገነናዊ የጸረ ኢትዮጵያ እምነቶቹ ውላጅ ከሆነው አመለካከቱ ተነስቶ ወድቃ የተነሳችውን የህዝብ የፍትህና የነጻነት ተምሳሌት የሆነችውን ባንዲራ “ጨርቅ ናት” በማለት እንዳልተሳለቀብን ዛሬ፣ የባንዲራ ቀን የሚል በዓል አዘጋጂቶ ያላንዳች ይሉንታ ኑ አክብሩ ይለናል። ባንዲራ ለሀገር ዳር ድንበር የተከፈለ መስዕዋትነት መግለጫ መሆኑ እየታወቀ፣ የሀገር ድንበር በየዓቅጣጫው እየቸበቸበ መለስ የባንዲራ ቀን ድግሴን አድምቁልኝ ይለናል።

ይህ ትዕይንት ግን ሶስት መቶ ሽህ ባንዲራዎች በመንግስት ኪሳራ እንዲያመርት ኮንትራት ከተሰጠው የመለስና የሸሪኮቹ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ከሚገኘው የትርፍ ጥቅም ሌላ የሚፈየደው አይኖረውም። ባንዲራ ማጣጣል በሥልጣን ላይ ለመቆየት ተብሎ በታሰበበት ወቅት ባንዲራን ማጣጣል፣ አሁን ደግሞ ያ የትም እንደማያደርስ በታየበትና ከሥልጣን የመነቀል አደጋ ፈጦ በመጣበት ወቅት በሥልጣን ከመሰንበት ሥሌት ተነስቶ ባንዲራ ማውለብለብ ከተራ ብልጣብልጥነት ያለፈ ትርግም እንደማይኖረው የኢትዮጵያ ህዝብ ይረዳዋል። እውነቱን ከሆነ፣ ወድቃ የተነሳችው ባንዲራ ለህዝብ ትርጉም የምትሰጠው ህዝብ ለዳር ድንበሩ መከበር፣ ለነጻነትና ለህትህ መስፈን ያለውን ቀናዒነትና ባለፈው የከፈለውን ወደፊት ሊከፍለው የተዘጋጀውን መስዕዋትነት የምትገልጽ ስለሆነች ነው። የሚወዳትም፣ የሚያፈቅራትም መለስ ጨርቅ ናት ብሎ ሲጥላት ለእዚህ ያበቃትም ለእዚህ ነው።

ይህንን ታሪካዊ፣ ሃገራዊና ህዝባዊ ባንዲራ ትርጉም ለአንድ አፍታ ሳይጋሩ፣ መለስና ጓደኞቹ የሚያውለበልቡትን አረንጓዋዴ፣ቢጫና ቀይ ቀለም ነገር በእነሱ እጂ ድሮም እነርሱው እንዳሉት ጨርቅ እንጂ ሌላ ትርጉም ከቶውንም ሊኖረው አይችልም። የዛሬይቱ የሃገራችን ገዥዎች ህዝብ ለባንዲራ ያለውን ከበሬታ በዕውን የሚጋሩ መሆናቸውን የሚታወቀው፣ ባንዲራውን ስላውለበለቡ ሳይሆን፣ከባንዲራው ጀርባ ለሚገኙ የህዝብ ፍላጎቶች ተገዥ ሲሆኑ ብቻ ነው። እነኝህን ፍላጎቶች የነጻነትና የህትህ መስፈን፣ የብሄራዊ ደህንነትና ጥቅም መጠበቅ ፍላጎቶች ናቸው። የመለስ አገዛዝ ደግሞ የማይታማበት ነገር ቢኖር እነዚህን የህዝብ ፍላጎቶች የማይጋራ መሆኑ ነው። በሃገራዊ ክህደት እየሰመጡ ነጻነትና ፍትህን እየረገጡ የኢትዮጵያን ባንዲራ ለማውለብለብ የተነሱትን መለስና ጓደኞቹ “በህግ አምላክ ወድቃ በተነሳችው ባንድዲራ” ባንዲራችንን ለቀቅ አድርጓት የሚላቸውም ለእዚህ ነው።

## ከደቡቡ የአገራችን ክፍል የተባረሩ የአማራ ተወላጆች ታፍሰው . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ተፈናቃዮቹ በአሁኑ ጊዜ ከስላሴ ቤተክርስቲያን ጀርባ እና የካቲት 12 አካባቢ በሚገኝ ሁለት የማጎሪያ መጋዘኖች ውስጥ እንዲገቡ ተደርጓል። ሰዎቹ ከቤት እንዳይወጡ፣ ከማንም ሰው ጋር እንዳይገናኙ በመደረጉ ስላሉበት ሁኔታ ለማወቅ ፈጽሞ አልተቻለም። ከአካባቢው የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ለተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን ቃለምልልስ የሰጡ ተፈናቃዮች እየተደበደቡ ምርመራ እየተደረገባቸው ነው። ከእነዚሁ ምንጮች የተገኙት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት መኢአድ ለተፈናቃዮቹ ባሳየው ተቆርቋሪነት ባገኘው ከፍተኛ የፖለቲካ ትርፍ የተበሳጨው ብአዴን ሰዎቹን ያለምንም ዝግጅት ከመኢአድ ግቢ አስወጥቶ ከማንም ሰው ጋር እንዳይገናኙ በማድረግ ግቢውን በወታደር እያስጠበቀ ነው።

የብአዴን ድርጊት ያስቆጣቸው አንድ የፖለቲካ ድርጅት መሪ ግለሰቦቹ ከተፈናቀሉት በላይ ብአዴን እስር ቤት ውስጥ መክተቱ ለሰዎቹም ለወገኖቻቸውም ሞት ነው ማለታቸውን ኢሳት በዘገባው ገልጿል።

ኢሳት በማያያዝም ከዛው አካባቢ በሁለት አይሲዙ የተሳፈሩ ሌሎች የአማራ ተፈናቃዮች ሰሞኑን አዲስ አበባ ይገባሉ ተብሎ ቢጠበቅም ይገባሉ በተባሉበት ቀን አለመግባታቸውን አስታውቋል። የተፈናቃየቹን ጉዳይ በቅርበት የሚከታተሉትን ሰው ጠቅሶ እንዳለው ተፈናቃዮቹ ከአካባቢው ተሳፍረው መንገድ መጀመራቸውን አረጋግጠዋል፤ይሁንና ከተወሰነ ሰአት በኋላ የት እንደደረሱ ለማወቅ ያደረጉት ሙከራ ሳይሳካ ቀርቷል። ተፈናቃዮቹ አዲስ አበባ መድረስ በሚገባቸው ሰአት ባለመድረሳቸውም ወያኔ ወደ ሌላ አቅጣጫ ወስዷቸዋል የሚለውን ግምት አጠናክሮታል።
ይህ በእንዲህ እንዳለ ሌሎች ከዛው አካባቢ ተፈናቅለው አዲስአበባ ገብተው የነበሩ አማሮች ካለፍላጎታቸው በፖሊስ ተገደው ወደ ደብረብርሃን ተወስደዋል - ሪፖርተር እንዳለው። ተፈናቃዮቹ ፍትህ ለማግኘት አዲስአበባ ብንመጣም የባሰ ግፍና በደል እየተፈጸመብን ነው ብለዋል።
እነኚሁ ተፈናቃዮች በዘር ጥላቻ ካበደው መለስ ዜናዊ ፍትህ እናገኛለን ብለው ነበር ባለፈው ሀሙስ መጋቢት 20. 2004ዓ/ም ወደ አራት ኪሎ ቤተመንግስት የሄዱት፣ነገርግን ያገኙት ምላሽ በፌደራል ፖሊስ ታፍነው ከፓርላማ ፊትለፊት ለመልሶ ግንባታ በታጠረው ግቢ ውስጥ መታጎርናና ያለፍላጎታቸው ወደ ደብረብርሃን መወርወር ነው።

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 በወጣቶች ከበብ ውስጥ ከቀሩት ጥቂት ተፈናቃዮች አንዱ ብሶታቸውን ሲገልጹ ሕጻናት ምግብ ስጡን እያሉ ነው ወደ ደብረብርሃን የተወሰዱት፣መፍትሄ ፍለጋ መጥተን ግፍና በደል እየተፈጸመብን ነው። የ22 ቀበሌ ህዝብ ሲፈናቀል መንግስት ተብዬዉ እንዴት ዝም ይላል?

ማለታቸውን ከሪፖርተር ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

ጉዳዩን አስመልክቶ መኢአድ ለዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ግልጽ ደብዳቤ ጽፏል፤መኢአድ በደብዳቤው በሕጋዊ መንገድ ከመንግሥት መሬት ተሰጥቷቸው፣ ይህንንም የሚያረጋግጥ ሕጋዊ ሰነድ በእጃቸው እያለ፣ ከዚህም ባለፈ በአካባቢው ቋሚ ሀብት ባፈሩበት ሁኔታ ላይ የሚገኙ ዜጐችን፣ በሕገወጥነት ፍርጃ ለረጅም ዓመት ከኖሩበትና ቤተሰብ ካፈሩበት ቀየ ማፈናቀልና ማሳደድ፣ እንዲሁም ያለ ምንም ካሳ ሀብትና ንብረታቸው በካድሬዎች ያለአግባብ እንዲወረስ ማድረግ፣ ለሕዝብ ቆሜያለሁ ከሚል መንግሥት በፍፁም የማይጠበቅ በመሆኑ፣ በዘር ጥላቻና ቂም ያበደው የመለስ ዜናዊ ቡድን በተፈናቃዮቹ ላይ የደረሰውን ኢፍትሃዊነት እንዲቀለብስ መኢአድ ጥያቄ አቅርቧል።

የክልሉን ውሳኔ ተከትሎ በተፈናቃዮቹ ላይ የደረሰውን በደልም መኢአድ እንዲህ ሲል ይገልጻል፡፡ ‹‹ነፍሰ ጡር እናት ሌሊት ወልዳ ሲነጋ የሰዓታት ዕድሜ ካለው ልጇ ጋር ከነፍራሿ ደጅ ተጥላለች፤ ነፍሰ ጡሮች ተሰደዋል፤ የስምንት ወር ዕድሜ ካላቸው ጨቅላ ሕፃናት ጀምሮ በርካታ ሕፃናት ከሚያጠቡ እናቶቻቸው ጋር አብረው ታስረዋል፤ የሚላስ የሚቀመስ አጥተው በረሃብ ተጠብሰዋል፤ በነፍስ ወከፍ እስከ 3 ሺሕ እግር ቡና ዛፍ፣ አቡካዶ፣ ማንጐ፣ ፓፓያና ሙዝ የተከለ እንዲሁም በርካታ የንብ ቀፎ የሰቀለው፣ በከብትና በዶሮ እርባታ ላይ የተሰማራው ገበሬ ያመረተውንና ያፈራውን ሀብትና ንብረት ጥሎ ጨርቁን በፌስታል አንጠልጥሎ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ ‘ምንም ይዛችሁ ስላልመጣችሁ ምንም ይዛችሁ አትሄዱም’ እየተባሉ ንብረታቸውን ሜዳ በትነው እንዲሄዱ ተደብድበዋል፤›› ብሏል በደብዳቤው፡፡

በርካታ የፖለቲካ ተንታኞች ድርጊቱ የዘር ፖለቲካው አስከፊ ውጤት ነው ሲሉ ሌሎች ወገኖች ደግሞ የአሁኑ እርምጃ የመለስ መንግስት ለአለፉት 20 አመታት በአማራ ህዝብ ላይ ሲፈጽም የነበረው ጥቃት ቅጥያ ነው በማለት ይገልጻሉ።

በደቡብ ክልል ፕሬዚዳንት በሽፈራው ሽጉጤ መመሪያ የተፈናቀሉ ከ20 እስከ 70 ሺ የሚጠጉ የአማራ ተወላጆች እንዳሉ መረጃዎች ያመለክታሉ።

## በኢንቨስት መንት ሥም ዜጎችን ከይዞታቸው የማፈናቀሉ ዘመቻ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ይፈናቀላል ተብሎ እንደሚገመትና ይህንን ውሳኔ በተቃወመው የአፋር ህዝብና በአገዛዙ መካከል የተፈጠረው ፍጥጫ ተባብሶ ሌላ ያልተጠበቀ የህዝብ አመጽ ሊቀሰቅስ እንደሚችል ስጋት ፈጥሮአል።

የሙቀት ደረጃው ሃይለኛ በሆነው የአዋሽ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚኖረው የአፋር ህዝብ ለራሱና ለሚያረባቸው ከብቶች ህልውና ከአዋሽ ወንዝ ርቆ መኖር እንደማይችል ለዘረኛዉ መለስ ዜናዊና ለክልሉ ባለስልጣኖች ያቀረበው አቤቱታ ሰሚ ከማጣቱም በላይ አባ ጸሃዬ የተባለው የመለስ ዜናዊ ተቀጢያ "መንግሥት ከፈለገ የአዋሽን ወንዝ ሞጀ ላይ በመገደብ አካባቢውን ወደ ምድረ በዳነት የመለወጥ አቅም እንዳለው በመናገር ህዝቡን ለማስፈራራት መሞከሩን የአካባቢው ሽማግሌዎች ይናገራሉ።

በሽንኮራ ልማት ሥም ለዘመናት ተከብሮ የኖረውን የዋልድባ ገዳምን ይዞታ ወያኔ ለመውሰድ እያደረገ ያለው ጥረት ተመሳሳይ ተቃውሞ ማስነሳቱን መዘገባችን ይታወሳል። ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ ባላቸው ቀረቤታና ታማኝነት ለኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፓቲሪያርክነት የበቁት አባ ፓውሎስ የሚመሩት ሲኖዶስ በዋልድባ ገዳም የተፈጠረውን ጥቃት እንደማውገዝ ፋንታ አገር ያወቀውንና ጸሃይ የሞቀውን ሃቅ በመሸፋፈን "መንግሥት የዋልድባን ይዞታ እንደማይነካ አረጋግጦልናል" የሚል የተሳሳተ መግለጫ ባለፈው ሳምንት ማሰራጨታቸው ህዝበ ክርስቲያንን እያነጋገረ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የሚታየው የህዝብ መፈናቀል በመላ አገሪቱ ቁጣን እየቀሰቀሰ ነው። በደቡብ ኦሞ ከ200 ሺ በላይ ህዝብ መፈናቀሉን ተከትሎ ከፍተኛ የጸጥታ መደፍረስ እየታየ ነው። በጋምቤላም እንዲሁ በክልሉ ለሚታየው ተደጋጋሚ የጸጥታ ችግር ዋናው መንስኤ የህዝብ መፈናቀል ነው።

ዜጎችን ከድንግል መሬታቸውና ታሪካዊ ቦታዎቻቸው እያፈናቀሉ በህንድ በቻይናና በአረብ ከበርቴዎች የማስያዙን ጥረት ህዝባችን በሙሉ በአንድነት ሆ ብሎ ካላስቆመ በስተቀር የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዘመኑን ጨርሶ ከስልጣን ሲወገድ አገራችን የምትከፍለው ዋጋ ቀላል እንደማይሆን ግንቦት 7 ሁሌም እያስጠነቀቀ መሆኑ ይታወቃል።

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ ቡድን ከደቡብ ያባረራቸውን ዜጎች በግዳጅ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

**ግንቦት 7 በእንግሊዘኛ** ባወጣው መግለጫ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጭካኔ በተሞላበትና ስብአዊነት በጎደለው ሁኔታ ዜጎች ኑሮአቸውን ከመሰረቱበት፤ ሃብትና ንብረት ካፈሩበት ቀያቸው ባዶ እጃቸውን እንዲባረሩ ማድረጉ እጅግ የሚያሳዝን እንደሆነ ጠቅሶ እንዲህ አይነት እርምጃ የተለመደ የቅምና የበቀል እርምጃ መገለጫ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የጥቃቱ ሰለባዎች ከደረሰባቸው ማህበራዊ ቀውስ በተጨማሪ በሰላም አብሮ እየኖረ ባለ ህዝብ መካከል ሆን ብሎ ግጭት ለመቀስቀስ የታለመ ሴራ ነው ብሎአል።

በጋምቤላ የተፈጸመውን ዘር ማጥፋትና በቅርቡ በአፋር እየተካሀደ ያለው መፈናቀል የሚያስከትለውን በዘር ላይ የተነጣጠሩ ጥቃቶች ግንቦት 7 በቅርቡ እንደሚከታተል የገለጸው መግለጫ እንዲህ አይነቶቹ እርምጃዎች ህዝቡን በገዛ አገሩ ባይተዋር የማድረግና አንገቱን በሃይል አስደፍቶ ለመግዛት የሚደረግ ጥረት አካል ነው ብሎታል።

ወያኔ ዜጎችን ከኑሮአቸውና ከንብረታቸው ከማፈናቀል አልፎ የእምነት ገዳማትን ለማጥፋት በዋልድባ እየፈጸመ ያለው ግፍ የአገሪቱንም ሆነ የአለም አቀፍ ህጎችን የሚጻረር ተግባር ስለሆነ አለም አቀፉ ማህበረሰብ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ የሚችለውን ጫና ሁሉ በማሳደር ከጥፋት ድርጊቱ ሊያስቆሙት ይገባል ያለው የግንቦት 7 መግለጫ ዜጎችም ቢሆኑ ይህ በአገራቸውና በወገኖቻቸው ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ በቸልታ መመልከት የለባቸውም በማለት ህዝቡ ሆ ብሎ ተነስቶ መብቱን እንዲያስከብር ጥሪውን አቅርቦአል።

በተያያዘ ዜና የግንቦት 7 የሴቶች ኮሚቴ በመለስ ዜናዊ ዘረኝነት ፖልሲ ምክንያት ከአገሯ ተሰዳ በሊባኖስ ትኖር በነበረቺው ወገናችን አለም ደቻሳ ላይ በቅርቡ የተፈጸመውን ጥቃት በመቃወም መግለጫ አውጥቶአል።

ኢትዮጵያውያን በአጠቃላይ በተለይም በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የሴቶች ፎረም በሊባኖስ አደባባይ በገዥዉ ፖርቲ የቆንስላ ጽ/ ቤት ፊት ለፊት በእህታችን ዓለም ደቻሳ ላይ የደረሰውን ጨካኝና ስብዓዊነት የጐደለው ድብደባና ማንገላታት ፤ እንዲሁም ሞት አጥብቀን እንቃወማለን ያለው የሴቶች ኮሚቴ መግለጫ በተመሳሳይ ሁኔታ በመካከለኛው ምስራቅና በመላው ዓለም በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ እየደረሰ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥስትና መንገላታት እናወግዛለን ብሎአል።

በኢትዮጵያ ያለው አምባገነን ፣ ጨካኝና ኢፍትሃዊ ሥርአት በፈጠረው የመልካም አስተዳደር ዕጦት፣ የፍትህ መዛባት፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ ሙስናና የኑሮ ውድነት፣ ዜጐች ወደ አጐራባች አገሮች ብሎም ወደ መካከለኛ ምሥራቅ፣ሰሜን አሜሪካና አውሮፖ አገሮች እየተሰደዱ ለከፋ ኑሮ አደጋ ተጋልጠው ይገኛሉ የሚለው መግለጫ፤ በተለይም በመካከለኛው ምሥራቅ በቤት ሠራተኛነት ለስደት የሚዳረጉ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ እህቶቻችን በሚኖሩበት አገር የሚደርስባችው መደፈር ግፍና በደል ለሕጋዊ ባርነት ዳርጓቸዋል ይህም ከአካላዊ ጉዳት እስከ አእምሮ መታወክ ለሚያደርስ ጉዳት እንዲሁም ሞት እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል በማለት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የፈጠረውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያው ቀውስ ያማርራል።

የግንቦት 7 የሴቶች ፎረም በወያኔ ቆንስላ ጽ/ቤት በር ላይ በአለም ደቻሳ ላይ የተፈጸመው ግፍና በደል የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ለአገራችንንና ለዜጎቿ ክብር ያለውን ንቀት አመልካች መሆኑን ጠቅሶ ዜጎች ሁሉ ይህንን የወያኔን እብሪት ለማስቆም መነሳት እንዳለባቸው በተለይም የማህበረሰባችን ግማሽ አካል የሆንነው ሴቶች የዚህ ብልሹ አገዛዝ ዋንኛ ተጠቂ መሆናችንን ተረድተን ችግሩን ለማስቆም እየተደረገ ያለውን የነጻነት ትግል ሳይውል ሳያደር መቀላቀል እና የነጻነት ቀናችንን ማቅረብ፤የባርነት ዘመናችንን ማሳጠር ይኖርብናል በማለት ጥሪ አቅርቦአል።

## በኢትዮጵያ ውስጥ እየደረሰ ያለው የሙብት ጥሰትና የህጋዊ ስርዓት መናጋት

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

መግለጫው በማያያዝም በቤንች ማጂ ዞን ምስኪን አርሶ አደሮችን በገፍና በግፍ ከመኖሪያ ቀዬአቸው በማፈናቀል የማባረሩ ርምጃ በአሁኒቷ ኢትዮጵያ የህግ የበላይነት ከስሞ ስርአት አልበኝነት የበላይነት ለመያዙ ዓይነተኛ ማስረጃ መሆኑን ጠቅሶ መድረክ ይህ ሁኔታ ሀገሪቱን ወደ አጠቃላይ ቀውስ ሊከታት ይችላል ብሎ እንደሚሰጋ ገልጿል።

በመጨረሻም መድረክ በመግለጫው የተቃውሞ ፖለቲካን ለማጥፋት የዜጎችን የግለሰብና የቡድን ሙብት እየረገጠ ያለውን የወያኔ ስርዓት በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ አግባብ ለመቀየር የሚያደርገውን ትግል በመደገፍ መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲገባ ለመላው ህዝብ ጥሪ አስተላልፏል።

በጉዳዩ ላይ አንድ የወያኔ ተቃዋሚ ድርጅት አባል በሰጡት አስተያየት ይህ ዘረኛና ግፈኛ የወያኔ መንግስት በቂም በቀል በመነሳት ህዝቡን በረሃብና በችግር ከመጥበሱ ባሻገር ሞራሉን በመስበር የመንፈስ ድቀት እንዲደርስበትና አንገቱን ደፍቶ እንዲገዛ ለማድረግ ተግቶ እየሰራ ነው።የግፍና የመከራ ብዛቱ ደግሞ ስርአቱ የፍጻሜው መጨረሻ ላይ መድረሱን አመላካች ነው።እናም ሁሉም ዴሞክራሲያዊ ሃይሎችና መላው ህዝብ ይህን ዘረኛና ግፈኛ የወያኔ ስርአት ለማስወገድ በጋራ መረባረብ ያለባቸው ወቅት ነው ዛሬ።ይህ ወቅት ካለፈ ግን የስቃይ መጠኑ እንደሚጨምርና ዘመኑም እንደሚረዝም ልብ ሊባል ይገባል ብለዋል።

## የመለስ ዜናዊ ቀኝ እጅ የሆነው ብርሃኔ ገብረክርስቶስ በአማሪካን አገር ያለውን የነዳጅ ማደያ ለመሸጥ የሽያጭ ማስታወቂያ መውጣቱ ተዘገበ

ህወሃት ስልጣን ከተቆጣጠረበት 1983 ጀምሮ እስከ አለፈው 2002 በአሜሪካን አገርና በበልጂዬም የመለስ ዜናዊ አምባሳደር በመሆን ለረጂም ጊዜ ሲያገለግል ቆይቶ በውጪ ጉዳይ ምንስትርነት ለተመደበው የደቡቡ ተወላጅ ሃይለማሪያም ደሳለኝ በሞግዚትነት የተቀመጠው ብርሃነ ገብረክርስቶስ በአሜሪካን አገር በዳላስ ከተማ የሚገኘውን ነዳጅ ማደያውን ለመሸጥ በሂደት ላይ መሆኑን በዳላስ የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው በላከልን መረጃ ገለጸ።

ብርሃኔ ገብረክርስቶስ ለረጅም አመታት ሲያንቀሳቅስ የነበረውን የነዳጅ ማደያ በ1.600 000 / አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ የአሜሪካን ዶላር/ ለመሸጥ ማስታወቂያ መውጣቱን ዜና ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ ያደረገው የኢትዮጵያ ሪቪው ድረገጽ ሲሆን የዝግጅት ክፍላችን ለማጣራት ባደረገው ሙከራ የመረጃውን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ ተችሎአል።

በዳላስ **ከተማ 6101 East Mockingbird Lane**, ላይ የሚገኘውን የብርሃኔ ገብረክርስቶስን ነዳጅ ማዲያ ንግድ ለማስተዳደር ሃይሉ መሳይ የተባለው የቀድሞ የወያኔ አባል ተቀጥሮ ሲሰራ እንደነበረ የገለጸው መረጃ፤ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በአሰሪው ብርሃኔ ገብረክርስቶስና በሰራተኛው ሃይሉ መሳይ መካከል በተነሳው አለመግባባት ሃይሉ ወደ አዲስ አበባ ተጠርቶ በእስር ላይ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ሪቪው ገልጾአል።

ብርሃኔ ገብረክርስቶስ በአሜሪካን አገር የወያኔ አምባሳደር ሆኖ ይሰራ በነበረበት ወቅት አሁን ከታረቃት ባለቤቱ ጋር ለፊቺ ፍርድቤት ቀርበው በስሙ አሜሪካን አገር ከተቀመጠው 40 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ኦንዲያካፍል ክስ ተመስርቶበት ፡" ገንዘቡ ለመለስ ዜናዊ በአደራ የተቀመጠ ነው" የሚል ማስተባበያ ሰጥቶ እንደነበረ በወቅቱ በሰፊው መዘገቡ ይታወሳል።

ብርሃኔ ገብረክርስቶስ ከመለስ ዜናዊ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ካላቸው ጥቂት የህወሃት ታማኞች አንዱ እንደሆነና በታማኝነቱ ምክንያት መለስ ና ባለቤቱ አዜብ መስፍን ከአገር ያሸሹትን በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የባንክ ሂሳብ ከፍቶ በውጪ አገር ሲያስቀምጥ የኖረ እንደሆነ ለህወሃት ቅርበት ያላቸው ምንጮች ይናገራሉ።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org